# አውቀው የሚሸፋፍኑት ሀቅ!

ከአማረ በላቸው

ውሻ በዓለም ላይ የምትጠይው ማንን ነው? ቢሏት፣ እኔ...!? እንደ ድሃ የምጠላው የለም አለች ይባላል። አባባሏ የሚነሳው ሰፈርተኛውን ነዋሪውን ሙጥኝ ብሎ ህይወቱ ከሀገሩ ሰው ጋር የተቆራኘውን የቆሎ ተማሪ ስታስቸግረው በዘንግ ወገቧን ለጥጦ የሚጥላት በመሆኑ ይሆናልና ብትጠላው አያስደንቅም፣ እስከ ዘለቄታው ጠላቴ ብላ ከፈረጀች ግን ስህተት ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ተማሪው ከትምህርቱ ፀጋ ሲያካፍል እሷም ቢሆን መጋራቷ አይቀርምና! ተማሪው ዕውቀቱን አካፍሎ ለመኖር የቆረጠ ወገን እንጂ ውሻንም ሆነ ጌታዋን በጠላትነት ፈርጆ /ውሾን ያየ ውሾ ..../ እያለ የሚሰብክ የሰዓት ቱጃር አይደለም። ከየት የመጣ ፍርሀት ነው መጠራጠሩ! ልመናውን ዘንግታ ያያቷን የቅድመ አያቷን ታሪክ አስታውሳ ከሆነ፣ በወገቧ ላይ ያረፈውን ዘንግ አሰላስላ ከሆነ፣ /ትላንት ዛሬ አይደለም/ ብሎታል ዘፋኙ። አሁንም የቆሎ ተማሪ ባየች ቁጥር ማንቧረቋን ከቀጠለች፣ ተማሪውን አባርረዋለሁ ብላ ከተነሳች፣ ምን ይደረግ መቼስ! ለውሻ የሮጠ ለውሻ የተደብቀ - ነፍሱን በጨርቅ የቋጠረ የለምና የሰው ልጅ ቆሞ መጠበቁ የግድ ነው። ተማሪውን ከዘገር ውሻዋንም ከጩኸት ለማላቀቅ ተማሪው ትምህርቱን እንዲያቆም፤ ውሻዋም ጩኸቷን እንድታቋርጥ፤ መምከር ሊሆን ነው። ለማትበላው እንጀራ መጮኹ የሚጠቅማት ነገር አለመሆኑን መምከሩ ጉዳት የለውም። ታዲያ ምክር ለውሻ ይሰራ ይሆን? ከሷም ዝምታን፣ ከጌታዋም ድጋፍን ለማስቆም መሞከር አጉል ምኞት ነው አይባልም። ቻይናን ያህል ያገር ጠላት፣ ወያኔን ያህል ቁማርተኛ አስቀምጦ መዝናናቱ ለውሾም እንደማይበጃት የታወቀ ነውና በቅድሚያ የጋራን ጠላት በጋራ መመለስ ያስፈልጋል ብሎ ቢመክሩ ምን ስህተት አለው። በእርግጥም ሀገሩን ወገኑን ክብሩን ማዕረጉን ያጣ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ በዓለም ተበትኖ በየሀገሩ መብቱ ተረግጦ፣ አንገቱን ደፍቶና መግቢያ አጥቶ እንዳለ እየተስተዋለ፣ ለመንግስቱ ሀይለማርያም የመፃፍ መብት ልሚገት ብሎ መነሳት በራሱ አሳፋሪ ነው። የሰው ልጆችን የማሰብ ነፃነትና ተግባራዊ የማድረግ መብት ወንጀለኞች ያሻቸውን እያደረጉ

እንዲኖሩ መፍቀድ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። በየዐረብ አገሮቹ በግርድናና በአሽከርነት የዐረብ መጫዎቻ መሆናቸው ሳያንስ፣ ባህላቸውን እንኳ እንዳያከብሩ በሳውዲና በተቀሩትም ስፍራዎች ተፅዕኖ እየተደረገባቸው በአፈና ተይዘው በየእስር ቤቱ እንዲማቅቁ የተዳረጉት ኢትዮጵያዊ ዜጎች ህይወት ከመንግስቱ የመፃፍ መብት ሳይከብድ ቀርቶ ነውን? የህግ አዋቂ መሆን ዕውነተኛ ፍርድን በወቅቱና በቦታው ሳይዛባ መተርጎም ማለት ነው። ስለፍትህ ስለህግ ክቡርነት እንቁም! ሲባል፣ በዝምድና በትውውቅ መስራት ብልግና ነው! የህሊና ዳኝነትን ሙልጭ አድርጎ መጣል አፀያፊ ልምድ ነው ማለታችን መሆን አለበት። ስለዚህም /አቅም የሌለው ይሙት!/ የሚለው የፀረ ህዝብ ሀይል — ኢህአፓን ወንጀለኛ ሊያስብለው ቢጥር፤ ቢያስገዝተው፤ ቢያስገድለው፣ ጥንትም የሚታወቅበት ትግሉ፣ አሁንም የቆመለት ግቡ ህዝባዊነት ነውና አንዲት ጋት ከህዝቡ ስሜት ፈቀቅ አያደርገውም።

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የገጠመውን ችግር የሚወጣበት መላ እያፈላለገ ነው እንጂ! የመንግስቱ ሀይለማርያምን የታሪክ ፀሀፊነት ብቃት የሚያደንቅበት ወቅት ላይ አይደለም። ገዝቶ ለማንበብም አቅሙ የለውም። መንግስቱ በኢትዮጵያ ህዝብ ችግር ድሮም ሲያፌዝ የኖረ አሁንም ለመቀለድ የተዘጋጀ መሆኑን ህዝብ እንዲያውቅለት ለማድረግ፣ ኢህአፓ በወሰደው እርምጃ መንግስቱም ሆነ ጀሌዎቹ ሊደሰቱ እንጂ! ሊከፉ አይገባም። በቀን ባንድ ጉርሻ የሚኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ለዚህ ሁሉ ቀልድ አመቺ ሁኔታ ላይ አይደለም።

ትብብር ከሀቅ፣ ትብብር ከልብ ከሆነ፣ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዚህ ያደረሱትን የደርግና የወያኔ ስብስቦች ፋይዳ እንደማይሰጣቸው መታወቅ ይኖርበታል። የህዝቡ ጠላቶች ኢላማቸውን በኢህአፓ ላይ ቢያነጣጥሩ፣ የሚያነጣጥሩት ለተገፋውና /አቅም የሌለው ይሙት/ ተብሎ ለተፈረደበት ህዝብ የቆመ በመሆኑ ነውና ችግር የለውም። አላማውን የተረዱለት ወገኖች ሚሊዮኖች ናቸው። ኢህአፓ ደጋግሞ ጉልበተኛውም፣ ብልሀተኛውም፣ ቋጣሪውም፡ ፎላዩም፣ አቅራሪዉም፣ በሙሉ ልብ ስለ መተባበር ካነሳ፣ መጀመሪያ በሀገር ውስጥ መንቀሳቀሱን አሳውቆ/መተባበሩን እዚያ! ያድርገው/ እያለ መክሯል። በእርግጥም በውጭ የሚደረገው መተባበር ከሰላማዊ ሰልፍና ከድጎማ የዘለለ ስለማይሆን፣ ይህ አይነቱ መተባበር መደረግ የሚገባው በድጋፍ

ድርጅቶች መካከል እንጂ! በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል አይደለም። የኢህአፓ መልዕክት ለኛ ለደጋፊዎቹ የተለየ ቢሆንም፣ ለጠቅላላው በንፁህ አዕምሮ ስለ ወገኑ ለሚጨነቅ ዜጋ ሁሉ የሚያቃጭል ጥሪ ነው። ኢህአፓ የድርሻውን ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን ደጋግሞ ገልጧል። ኢህአፓ ሁልጊዜ የህዝቡንስሜት ጠብቆ የሚጓዝ በመሆኑም የህዝብን ጥቅም በራሱ ጥቅም ለውጦ የታየበት ዘመን የለም። ህዝብ ባይደግፈው ኖሮ ኢህአፓ መኖር መቻሉ አስተማማኝ አይሆንም ነበር። ምክንያቱም ገዳዮቹ ብዙ አውርተዋላ፣ ብዙ ፎክረዋላ! ብዙ ሰቆቃ፣ ግድያ ፈፅመዋላ! ደርግ በቀይ ሽብር ሁሉንም ነገር ጨረስኩ ብሏል። ወያኔም እሬሳውን ሳወጣ ተመልከቱኝ፣ ከዚህ በሁዋላ ኢህአፓ የሚሉት ፓርቲ አይኖርም ብሎ ቃል ገብቷል። ለአጃቢዎቹ ምሎ፣ ተገዝቶ፣ እንዴት አድርጎ ነው ኢህአፓ አለ ሊል የሚችለው። ችግር ሆኖበታል።

አሁን ደግሞ የመንግስቱ ደጋፊዎች ኢህአፓ የለም ብለው ሊያሽካኩ ሲዳዱ፣ መኖሩን ሲያሳያቸው ይናደዳሉ። ህዝባዊ ፍቅር የሌላቸው የፖለቲካ ጠበብቶች ጀሌ ማሰለፍ ቅድሚያ የሚሰጡት ጥበብ ነውና፣ ማዋዛታቸውን ቆጠብ አድርገው፣ ከማስመሰሉ ተገተው፣ በሜዳ ላይ የሚታይ፣ ከህዝባችን ጋር ያለ ስራ እንስራ ሲሏቸው፣ ያሰለፏዋቸውን የፈረደባቸው ጀሌዎች አሰማርተው ያሰድባሉ። ኢህአፓ አርባ ዓመት ሞላው! አረጀ አፈጀ! ጡረታ መውጣት አለበት ወዘተ. ሲሉ ይውሉና አንድ ነገር በመጣ ጊዜ፣ ይኸ የኢህአፓ ስራ ነው እያሉ መላቀስ ይጀምራሉ። የለም፣ ሞቷል፣ ተቀብሯል፣ ያሉት ኢህአፓ ከየት መጥቶ ነው ሊያሸብራቸው የበቃው? ኢህአፓ በኛ በደጋፊዎቹ እምነት ብቻ ሳይሆን በህዝቡ ልብ ውስጥ ሰርፆ የሚኖር መሆኑ ካልተገለፀላቸው ለምን ሞቷል ያሉትን አለ ይሉታል።

ኢህአፓ ከመጀመሪያው ጀምሮ የህዝብን ፍላጎት ለመተርጎም የተነሳ በመሆኑ፦ የትግል ልምዱን ያካበተው በከተማ ጎዳናዎች የአመፅ ሰልፎች ላይ ነው። በሜዳ ውስጥ ለወገናቸው ሲሉ የታጠቁ የህዝብ ልጆች መስዋዕት በመሆን በፈፀሙት ገድል ላይ በመነሳት ነው። ኢህአፓ ኢትዮጵያ ሲል፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ሲል፣ ልዩ ትርጉም አለው። ህይወትን የማይሸሽጉበት፣ ዘመድን ለይቶ በተሻለ ስፍራ የማያስቀምጡበት፣ በህዝብ ጠላቶች ዘዴና ተንኮል የማይተበተቡበት፣ ልዩ የመስዋዕትነት ዋጋ ማለቱ ነው። ስለዚህም ካዳራሽ ጭብጨባ

የተገኘ ፋይዳ አለ ብሎ ሊያምን አይችልም። ኢ.ህአፓ እስካሁን ድረስ አልተመለሱም ብሎ  የሚያምንባቸው የህዝብ መፈክሮች ቀጣይ ትግል የጠየቁ ናቸው። እነሆ!

1. **ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት** — በወቅቱ የወታደሩን አምባገነንነት በመጠኑም ቢሆን ይገታል ተብሎ የቀረበ ህዝባዊ ጥያቄ ሲሆን፣ በትግል ውስጥም ኢ.ህአፓ በርካታ አባላቱን ያጣበት ነው። እንጂ! ስልጣኑ ለኔ ይገባኛል ብሎ አልተሟገተም። ይኸ ለስልጣን ያሰፈሰፉ ክፍሎች የሚያዛምቱት ተራ አሉባልታ ነው። ኢ.ህአፓ፣ ከአዛውንቶች፣ ከወጣቶች፣ ከሴቶች፣ ከአስተማሪዎች፣ ከሰራተኞች፣ ከወታደሮች ወዘተ. በጊዜው ከነበሩ ማህበራት ሁሉ የተውጣጣ ጊዜያዊ አመራር ይፈጠር አለ እንጂ! ወታደሩ ብቻ የታሪክ አጋጣሚ በሚል ለስልጣን የሚያደርገውን ርኩቻ ተቃወመ እንጂ! እኔ ልቀመጥ አላለም። ይኸ ጥያቄ አሁንም ያልተፈታ ችግር ስላለ የሚነሳ ነው። በብዙዎች ዘንድ የሚቀርበውን /የሽግግር መንግስት/ን ጥያቄ ያስተውሷል።

2. **የዲሞክራሲ መብት ያለገደብ** - በወቅቱ ደርግንና አጋር ድርጅቶቹን ያበሳጨ ነበር። ይሁንና ጥያቄው እስካሁንም ድረስ  ያልተመለሰ በመሆኑ የህዝብ ትግል እየተቀጣጠለበት ያለ ነው።

3. **መሬት ላራሹ** - ትልቁና ዋናው ከተማሪው ማህበር ጀምሮ ሲንከባለል የቆየ ጥያቄ ነው። ደርግ መሬት የመንግስት ነው ብሎ አውጆ፣ እንደፈለገው ህዝብን ሲያንገላታ ቆየ እንጂ! ምላሽ አላስገኘም። ወያኔም ጭራሽ መሬትን ለባዕዳን ባለሀብቶች መሸጥ ያዘ እንጂ! የህዝብን ጥያቄ አላከበረውም።

እናም በዚህ ሁሉ ምክንያቶች ኢ.ህአፓ አሁንም ከህዝብ ጋር ሆኖ ለመታገል ቢወስን ጠላት እንጂ! ወዳጅ ሊበረግግ አይገባም። አንዳንዶች እንደሚሉት ኢ.ህአፓ ዘላለም በትግል መቆየትን መርጦት ሳይሆን፣ የህዝቡ ጥያቄዎች አንዳቸውም የተመለሱ ባለመሆናቸው ህዝቡን ጥሎ፣ በራሱ ጥቅማ ጥቅሞች ተታሎ፣ ከትግል መድረክ ማፈግፈግ ወንጀል

በመሆኑና፣ ህዝቡን አጋፍጦ የሚሸሽ፣ ለባዕዳን የሚዋሽ ወይም በፍርሀት የሚሿሸሽ ፓርቲ ባለመሆኑ፣ ጥንታዊው የኢትዮጵያዊነት፣ የአርበኝነት መንፈስ እንዲታደስ የሚደረገውን ጥረት በወክንድ የተጠናከረ አሰራር ህዝባችንን ለመታደግ ከመዘጋጀትና ህዝብን አስተባብሮ ከመነሳት ውጭ ሌላ አማራጭ አለ ብለን አናምንምና ምንጊዜም ደጋፊዎችህ ከጎንህ ነን!

የኢትዮጵያ ህዝብ አቸናፊ ነው!!